# ግልፅ አሠራርና ተጠያቂነት እንዲሰፍን እንሰራለን!!



# ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት መቋቋሚያ አዋጆች ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች




ዋናው መ/ቤት ፡ –

ባህር ዳር

⇒ ቀበሌ ፡ – 16

⇒ ስልክ ቁጥር ፡ –

0582201992/0634/2265734

⇒ ፋክስ ቁጥር ፡ – 0582201694

⇒ ፖስታ ሳጥን ቁጥር ፡ – 479

⇒ ድረ–ገጽ ፡ – www.anrs.oag.gov.et

⇒ ማህበራዊ ድረ-ገጽ:- ANRS office of auditor general

በአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

## የመ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ

## 1. ተልዕኮ

የኦዲት ስራን ገለልተኛ በሆነ መንገድ በማከናወን ለም/ቤቱ እና ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተጨባጭ መረጃና የሙያ ምክር ይሰጣል፡፡

የኦዲት ሙያ ሽፋንና ጥራት በማሳደግ በመንግስት ስራ ውስጥ ተጠያቂነትና አርአያነት ያላቸው ልምዶች እንዲስፋፉ ይሰራል፡፡

## 2. ራዕይ

በክልሉ የመንግስት መ/ቤቶች የአሰራር ግልፅነት፣ ውጤታማነትና የፋይናንስ ተጠያቂነት እስከ 2022 ዓ.ም ሰፍኖ ማየት፡፡





- **ተጠያቂነት [Accountability]፡-** ግዴታችንን በአግባቡ በመወጣትና ተገቢ ጥያቄ ሲቀርብልን አስፈላጊውን ማብራሪያ በመስጠት የመ/ቤቱን ተልኮና ግቦች እናሳካለን፡፡

- **ፈጠራ እና ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ[creativity and continuous improvement:-** ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለላቀ ራዕይ ይጥራል፣ በላቀ አመለካከት፣ እምነት እና እሴቶች ላይ ያተኩራል እና ሁልጊዜም የላቀ የውጤታማነት ደረጃን ያሻሽላል፡፡

- **ሙያዊ ቁርጠኝነት [Professional comittement]፡-** የመ/ቤቱን ራዕይ፣ ተልኮ እና እሴት ለማሳካትና ከሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ ያላንዳች ቅድመ ሁኔታና ተነሳሽነት የህዝብን

**ማንኛውም የኦዲት ሂደት የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት ማድረግ አለበት**

## የመ/ቤቱ እሴቶች [core values)

- **የሙያ ብቃት [professional competence):-** በተከታታይ ትምህርት ራሳችንን በመገንባት ፣ የሙያ ደረጃውንና ስነ–ምግባሩን አክብረን በመስራት የደንበኞችን አመኔታ የሚያሳድግ የላቀ ሙያዊ አገልግሎት እንሰጣለን ፡ ፡

- **ሚዛናዊነት [objectivity):-** ህግን መሠረት በማድረግ በብቃትና ጥራት በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ተመስርተን ያለአድልኦ ሚዛናዊነትን ጠብቀን ለውጤት እንሰራለን ፡ ፡

- **ቅንነት [integrity]፡–** ስነ–ምግባራችንን ጠብቀን ሥራን ማዕከል ባደረገ መግባባትና መከባበር ለላቀ ውጤት እንሰራለን ፡ ፡

- **የቡድን ሥራ [team work]፡–** በግልፅና በጋራ እየሠራን በመማማርና በመደጋገፍ የመ/ቤቱን ተልዕኮና ግቦች እናሳካለን ፡ ፡



የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የመስሪያ ቤቱ ዓላማዎች

መስሪያ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 186/2003 መሰረት የሚከተሉት አበይት አላማዎች ተሰጥቶበታል ፡ ፡

1. የክልሉን ዕቅድና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ስርዓት መመስረትና ማጠናከር ፤
2. የክልሉ መንግስት ገንዘብና ንብረት በሕግ መሰረት መሰብሰቡን ፣ መጠበቁን እና በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ፤
3. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲዳብር ጥረት ማድረግ ፤
4. የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች ሂሳብ ኦዲት የሚደረግበትን ደረጃ ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል የሚሉ ናቸው ፡ ፡

**ኦዲት ነፃና ገለልተኛ ግምገማ ነው፡፡**

## የመ/ቤቱ ስትራቴጂካዊ የትኩረት መስኮች

1. ተቋማዊ አቅም ግንባታን ማሳደግ
2. የኦዲት ጥራትን ማረጋገጥ
3. የኦዲት ሽፋንን ማሳደግና
4. የኦዲት ኮምንኬሽን ማሳደግ ናቸው፡፡

## የሚጠበቅ ስትራቴጂካዊ ውጤት

- ፋይዳ ያለው የኦዲት አገልግሎት እና ግንዛቤው የዳበረ

**በኦዲት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ የማይወስዱ አካላት ተጠያቂ የሚያደርግ ሥርዓት መጠናከር አለበት፡፡**

ህብረተሰብ መፍጠር፡፡





ከ] በየደረጃው ባሉ የፍትህ አካላት በሕግ የተያዙ የኦዲት ግኝቶች ያሉበት ደረጃ በአብክመ ፍትሕ ቢሮ እንዲሁም በፖሊስ ኮሚሽን ተጠቃለው የአፈፃፀም ሪፖርት ለዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በየሦስት ወሩ እንዲደርሰው ይደረጋል፤ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትም አተገባበሩን እና ከተጠቀሱት አካላት ያገኘውን የግኝት አመላለስ ማስረጃ አካቶ ለክልሉ ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል የሚሉት በዚህ የማሻሻያ አዋጅ የተካተቱ ዋና ዋና ነጥቦች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ መ/ቤቱ ከተቋቋመበት 1986 ዓ.ም ጀምሮ ባለፉት 29 ዓመታት ማሻሻያ የተደረገባቸው የመ/ቤቱ መቋቋሚያ አዋጆች መነሻቸው የመ/ቤቱን መወቅራዊ አደረጃጀት መስፋት ፣ የመ/ቤቱን ሙያዊ ነፃነትና ገለልተኝነት ከማስጠበቅ አንፃር ፣ የመ/ቤቱ ተጠሪነትና የሠራተኞች አሠተዳደር ለውጥ መኖር እንዲሁም የኦዲት ሽፋንን ከማሳደግ

**ኦዲት ከማንኛውም አሉታዊ ተፅኖ ነፃ በሆነ መንገድ ሊሰራ ይገባል፡፡**

ለ] የመ/ቤቱን ስልጣንና ተግባር በተመለከተ ፤

በአዋጅ ቁጥር 267/2011 በክፍል ሁለት ‹‹የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር” በሚመለከተው የአዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 ስር በፊደል ተራ ኘ] ላይ ተደርጎ የነበረው ማሻሻያ ሃሳብ ወጥቶ ፊደሉ ባለበት ሆኖ በሚከተለው ሁኔታ ተሻሽሏል፡ ፡

ኘ] የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ኦዲተር መ/ቤት በክልሉ ውስጥ ለሚኖሩና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እና የድርጅት የምስክር ወረቀት ለማግኘት መስፈርቱን አሟልተው ለሚያመለክቱ ባለሙያዎች በኦዲት ሙያ ወይም በሒሳብ አያያዝ ሥራ መሠማራት የሚያስችላቸውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እና የድርጅት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ይከታተላል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሠርዛል፣ ስልጠናና ምክር ይሰጣል፣ ጥፋት ተፈጽሞ ሲገኝ የድስፕሊን ክስ ይመሠርታል፣ ወይም በሕግ አግባብ እንዲጠየቁ ለሚመለከተው የፍትሕ አካል ጉዳዩን ያስተላልፋል በሚል ተደንግጓል፡ ፡

ሐ/ በአዋጅ ቁጥር 186/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል ተራ ከ] ቀጥሎ ፊደል ተራ ኸ” እንደሚከተለው አዲስ ተግባርና ኃላፊነት ሆኖ ተጨምሯል፡ ፡





## የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ የሰራባቸው የመቋቋሚያ አዋጆችና ማሻሻያዎች ፤

ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ሃገራችን የፌደራል ስርዓት ተግባራዊ ማድረጓን ተከትሎ በማዕከላዊነት ደረጃ ተቋቋመው የነበሩ ልዩ ልዩ ተቋማት በክልሎቹ ደረጃ እንዲቋቋም የተደረገበት ጊዜ ነበር በመሆኑም የኦዲት መ/ቤቶችም በፌደራልና በክልል መንግስታት ደረጃ እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡ ፡

በዚህም መሰረት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ኦዲተር መ/ቤት በሐምሌ ወር 1995 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 6/1986 እንዲቋቋም ምክንያት ሆኗል፡ ፡ የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት በሽግግር መንግስቱ ወቅት በአዋጅ ቁጥር 6/1986 እንዲቋቋም ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ለሩ ጊዚያት የመቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያዎች የተደረጉለት ሲሆን እነሱም አዋጅ ቁጥር 6/1988፣ አዋጅ ቁጥር 98/1996፣ አዋጅ ቁጥር 186/2003 እና አዋጅ ቁጥር 267/2011 የሚሉት ተጠቃሽ ሲሆኑ የመጨረሻዎቹ ሁለት አዋጆች በአሁኑ ጊዜ በስራ ላይ የሚገኙ ናቸው፡ ፡ በተለያዩ ጊዚያት የተደረጉት የመቋቋሚያ አዋጁ ማሻሻያዎች ከተቋሙ ተጠሪነት፣ ገለልተኛነት፣ ተደራሽነትና የተሰጡትን ተግባርና ሃላፊነቶች የማስፋትና የመቀየር ሁኔታዎችን መሰረት ተደርጎ የተካሄዱ ናቸው

## የክልል ሦስት የሽግግር መስተዳደር የኦዲት መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 6/1986 የያዛቸው ዋና ዋና ስልጣንና ተግባራት ፣

የክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 6/1986 ሲቋቋም የሚከተሉት ዓላማዎችን በመያዝ ነበር ፡ –

- የክልል ሶስት የሽግግር መስተዳድር ም/ቤት ገንዘብና ንብረት ነክ የሆኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ያወጣቸውን አዋጆች ፣ ደንጋጌዎች ፣ ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ፣ የክልሉ ሀብትና ንብረት ከምዝበራና ከብክነት ተጠብቆ በተገቢው መንገድ መያዙን ለማረጋገጥ ፣
- ማናቸውም በክልሉ ሥር የሚገኝ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የክልሉ የፋይናንስ ቢሮ በሚፈቅደው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የሚጠቀም መሆኑን ለማረጋገጥ ፣
- ተመርማሪው መ/ቤት ያወጣውን ፕሮግራም በቅልጥፍናና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በማከናወን የሚጠበቅበትን ግብ ማሟላቱን ለማረጋገጥ ፤
- በምርመራው ወቅት በሚገኘው ውጤት ላይ ተመስርቶ ለተመርማሪው መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት በሚያስተላልፈው የሂሳብ ሪፖርት የተከሰቱ የአሰራር ግድፈቶች እንዲታረሙ ወይም እንዲስተካከሉ ለማድረግ ፣





### ሀ. ትርጓሜን በተመለከተ

በአዋጅ ቁጥር 186/2003 ዓ.ም በአንቀጽ 2 እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 267/2011 **በአንቀጽ 2 ስር ከተዘረዘሩት ትርጓሜዎች** በተጨማሪ የሚከተሉት ቃላት እና ሀረጎች በአዲስ ተጨምረዋል ፡ ፡

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፡ –

1. **የተፈቀደለት ኦዲተር"** ማለት የተፈቀደለት ኦዲተር ሆኖ እንዲሠራ በአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት የኦዲት ሙያ ብቃት ማረጋገጫ እና የድርጅት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ለማለት ነው ፡ ፡
2. **የተፈቀደለት ሒሳብ አዋቂ"** ማለት የተፈቀደለት የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ እንዲሠራ በአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት የሒሳብ አያያዝ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እና የድርጅት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ለማለት ነው ፡ ፡

**በኦዲት ሥራ የሚደረስባቸው መደምደሚያዎችና የሚቀርቡ የማሻሻያ ሀሳቦች ሁሉ በበቂ የኦዲት ማስረጃ ሊደገፉ ይገባል።**

## የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ ፣ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 287/2015 ፤

አዋጁ የወጣበት ዋና ዓላማ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ኦዲተር መ/ቤት የጥራት ደረጃውን ጠብቆ የኦዲት ሽፋኑን ለማሳደግ በመስሪያ ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ውስጥ የማያሰሩ ወይም ጊዜውን የማይዋጁ አንቀጾችን ማሻሻል ተገቢነት ያለው ሆኖ በመገኘቱና እሱም በአዋጅ ቁጥር 186/2003 ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 267/2011 ዓ.ም ውስጥ ተግባርና ኃላፊነትን ለመወጣት ምቹ ያልሆኑ ድንጋጌዎችን ማሻሻል እና የኦዲት መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የመረጃ ልውውጥ ለማጠናከር እና ተጨማሪ አንቀጽ ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

በዚህም መሠረት የአማራ ክልል ምክርቤት በተሻሻለው የክልል ህገ–መንግስት አዋጅ ቁጥር 59/1994 አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 እና 8 ድንጋጌዎች መሠረት የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ማቀቋቀሚያ አዋጅ የማሻሽያ አዋጅ ቁጥር 287/2015 አውጥቷል፡፡

በዚህ አዋጅ በአብዛኛው በአዋጅ ቁጥር 267/2011 በሚገኙ አንቀጾቹ የተደረጉ ማሻሽያወቹ ከዚህ በታቹ የተገለጹት ናቸው፡፡





- ከዚህ በላይ የተመላከቱ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስም በአዋጁ አንቀፅ 9 ላይ መስሪያ ቤቱ በርካታ ሥልጣንና ተግባራት እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡
- በተለይም በአንቀፅ 9 (2) ላይ የተመላከተው የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር የክልሉ ሽግግር መንግስት ወይም የመንግስት መ/ቤቶች ከ100,000 ብር በላይ የሚጠይቅ ስራ በተቋራጭነት ለግል ተቋማት ከሰጡ ዋና ኦዲተር መ/ቤቱ ኦዲት ማድረግ የሚችል ሲሆን የብር መጠኑ ከተጠቀሰው ገንዘብ በታች ሆኖ ነገር ግን በስራው ላይ ወንጀል ስለመፈፀሙ በቂ መረጃ ካለ የተቋራጮችን ሂሳብ መመርመር የሚያስችል ስልጣን እንደነበረው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ አዋጅ መሰረት በልዩ መልክ የሚታየው ሌላው ጉዳይ መ/ቤቱ ለማዕከላዊ የሽግግር መንግስት(የፌደራል መንግስቱ) የዓመቱን ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች በማጠቃለል እንዲያቀርብ የሚጠየቅ መሆኑ ነው፡፡ ዋና ኦዲተር መ/ቤቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በክልል ሠስት የሽግግር መስተዳድር ምክር ቤት አዋጅ ቁጥር 6/1986 ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ለአራት ጊዜያት የመቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ የተደረገለት ሲሆን እነሱም አዋጅ ቁጥር 6/1988 ፤ አዋጅ ቁጥር 98/1996 ፣ አዋጅ ቁጥር 186/2003 እና በአዋጅ ቁጥር 267/2011 እንዲሻሻል የተደረገባቸው ናቸው፡፡

## የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት የመጀመሪያው የመቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 6/1988 ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 6/1988 የታወጀው የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስትና የክልሎች ሕገ-መንግስት መፅደቅን ተከትሎ በሀገሪቱና በክልሉ ለመጀመሪያ ጊዜ የህዝብ ምርጫ ተደርጎ መንግስት ከተመሰረተ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት የክልሉ ህገ መንግስት አንቀፅ 49 [3] [1] መሰረት ይህ አዋጅ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 99 የዋና ኦዲተር መ/ቤት በዝርዝር አዋጅ ስልጣንና ተግባሩ ተወስኖ እንደሚቋቋም በሚደነግገው መሰረት ዋና ኦዲተር መ/ቤት በዚህ አዋጅ መቋቋም ችሏል፡፡

- በዚህ የማሻሻያ አዋጅ አንቀጽ 4 ላይ የመ/ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅር አስመልክቶ በነባሩ አዋጅ ቁጥር 6/1986 ላይ መ/ቤቱ ዋና ኦዲተሩን ጨምሮ ምክትል ዋና ኦዲተርም እንደሚኖረው ይገልፅ የነበረውን በማሻሻል በምክትል ዋና ኦዲተሩ ፈንታ የተለያዩ መምሪያ ኃላፊዎች እንደሚኖሩ ይደነግጋል፡፡
- በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 [3] መሰረት የዋና ኦዲተሩ ተጠሪነት ለክልሉ ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና ለርዕሰ መስተዳድሩ እንደሆነ ይገልፃል፡፡
- ከመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር አንፃር በአዋጁ አንቀጽ 8 [14] ላይ የተመላከተው የዓመቱን ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች በማጠቃለል ለክልሉ





- በዚህ አዋጅ ተመሥርተው በዋና ኦዲተር መ/ቤቱ የሚዘጋጁ ሪፖርቶች በዋና ኦዲተሩ ላይ የፍታሔርም ሆነ የወንጀል ክሶችን ለመመሥረት በጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ ስለመሆኑ ፣
- ኦዲተሮች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ሠፍራና ጊዜ የጸጥታ ችግር ሲያጋጥማቸው ወይም እንደሚገጥማቸው በመ/ቤቱ ሲታመንበት ዋና ኦዲተሮች ገለልተኛ የደህንነት ጥበቃ እንዲደረግላቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያለባ/ቸው ስለመሆኑ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**በነባሩ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀጽ 24 «ጥፋትና ቅጣት በሚል በተመለከተው አንቀጽ ስር ንዑስ አንቀጽ 2 በሚከተለው ሌላ አንቀጽ ተተክቶ የቀድሞው ንዑስ አንቀጽ 2 ወደ 3 እንዲሸጋሸግ ተደርገኋል፡፡**

- ንዑስ አንቀፅ 2 የያዘው ሃሳብም ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ [1] ስር የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆነው ጥፋቱን የፈፀመው ሰው ተሿሚ የሆነ እንደሆነ በሾመው አካል አማካኝነት ከስልጣን እስከማንሳትና ተጨማሪ እርምጃ ሊወሰድበት እንደሚችል የሚገልፅ ነው፡፡
- በተጨማሪም ንዑስ አንቀጽ 4 በዚህ የማሻሻያ አወጅ ላይ ሌላ አዲስ የተጨመረ አንቀፅ ሲሆን ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ [3] ስር የሰፈሩት

**ኦዲተሮች በኦዲት የሥራ ሂደት ወቅት ማንኛውንም መረጃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡**

- በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 267/2011 ላይ ግን የኦዲት ተደራጊ ተቋማትን ጨምሮ በየደረጃው የሚገኙ የአካባቢው የአስተዳደር አካላትንም ጭምር ግዴታዎች ያሉባቸው ስለመሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

**በነባሩ አዋጅ ቁጥር 186/2003 ያልነበሩና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 267/2011 እንዲካተቱ ከተደረጉት ተግባራትና ግዴታዎች መካከል ከዚህ በታች የተገለጹት ይገኙበታል ፡፡**

- ዋና ኦዲተሩን ጨምሮ በኦዲት መ/ቤቱ የሚሠሩ ሁሉም ባለሙያዎች ከሀገር አቀፍ የሙያ ስነ–ምግባር ደንብ ጋር በተገናዘበ ሁኔታ የሚያወጣውን የሙያ ስነ–ምግባር መመሪያ አክብረው የመሥራት ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ፤
- በመ/ቤቱ ውስጥ ተቀጥረው ወይም ተመድበው የሚያገለግሉ እና የሙያ ፈቃድ ይዘው በክልሉ የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ውስጥ በውጭ ኦዲተርነት ተሰይመው የሚያገለግሉ የግል ኦዲተሮች ዋና ኦዲተሩ ከሀገር አቀፍ የሙያው ስነ ምግባር ደንብ ጋር በተገናዘበ ሁኔታ የሚያወጣውን የሙያ ስነ–ምግባር መመሪያ አክብረው የመስራት ግዴታ አለባቸው፡፡
- በፍርድ ቤት ካልታዘዘ ወይም በዋና ኦዲተሩ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም የመ/ቤቱ ተሿሚ፣ ባለሙያ ወይም ሰራተኛ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 9 እና አንቀጽ 13 መሰረት ውክልና በተሰጠው





## የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት 2ኛው የመቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 98/1996

**በዚህ የ2ኛ ዙር የማሻሻያ አዋጅ ትኩረት የተደረገበት ዋናው ጉዳይ የክልሉን ዋና ኦዲተር መ/ቤት የሙያ ነፃነት ይበልጥ ማረጋገጥ የሚል ነው፡፡**

- ይህም በአንቀጽ 10 ላይ የተደነገገው ዋና ኦዲተሩ እና ምክትል ዋና ኦዲተሩ ከፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ገለልተኛ እንዲሆኑ ማስቀመጡ፣
- ከተጠሪነት አንፃር መ/ቤቱ እና ዋና ኦዲተሩ በአንቀጽ 12 መሠረት በቀጥታ ለምክር ቤቱ ተጠሪ የተደረገ ሆኖ ምክትል ዋና ኦዲተሩ ደግሞ ለዋና ኦዲተሩ እና ለምክር ቤቱ ተጠሪ እንዲሆን መደረጉ፣
- በአዋጅ ቁጥር 98/1996 የመ/ቤቱን ተቋማዊ ነፃነት ለማረጋገጥ በአዲስ መልክ ከተካተቱ ጉዳዮች መካከል የዋና ኦዲተሮችን የሥራ ዘመንን የሚመለከተው እና ዋና ኦዲተሮች ከኃላፊነት የሚነሱበት አግባብ በግልጽ ማመላከቱ፣
- በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 13 (1) መሠረት የዋና ኦዲተሩና ምክትል ዋና ኦዲተሩ የሥራ ዘመን አሥራ ሁለት ዓመት እንዲሆን መደንገጉ እና ምክር ቤቱ ካመነባቸው ለ2ኛ ጊዜ እንዲሾሙ ሊያደርግ እንደሚችል መገለጹ፣
- በተጨማሪም ዋና ኦዲተሮቹ ከኃላፊነት የሚነሱበትን ሁኔታ በግልጽ መደንገጉ ሲታይ ይህ አዋጅ ከመነሻውም የመ/ቤቱን የሙያ ነፃነት ይበልጥ የሚረጋገጥ ሐሳብ ያለው መሆኑንና በዕርግጥም ተቋማዊ ነፃነትን ለማረጋገጥ

**በዚህ አዋጅ ማሻሻያ የተደረገባቸው ሌሎች ስልጣንና ተግባሮችን ስናይ፡**

- የመ/ቤቱን ኦዲት የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት ከማስፋት አንፃር የክልሉ መንግሥት መ/ቤቶች ከዕርዳታ ሰጪ አካላት በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ የሚያገኙት ብድር ወይም የዕርዳታ ሒሳብ በተራድኦ የሒሳብ መደብ እየተያዘ ኦዲት መደረግ እንዳለበት የተደነገገበት መሆኑ፣
- የዋና ኦዲተር መ/ቤትን ሥልጣንና ተግባርን በሚመለከት በአንቀጽ ገ (2) (ሠ] ላይ እንደተመለከተው የግል ተቋራጮች ከክልሉ መንግስት ጋር የሥራ ውል ሲገቡ ሒሳቡን ኦዲት የማድረግ ሥልጣኑ በነበረው እንዲቀጥል የተደነገገ ሲሆን ውል የተገባበት የገንዘብ መጠን ግን ወደ 500,000 ብር ከፍ እንዲል በአዋጁ ማሻሻያ የተደረገበት እንደነበረ ለመረዳት ተችኋል፡ ፡

**ጥራቱንና ወቅታዊነቱን የጠበቀ የኦዲት ሪፖርት ተጠያቂነትን ያጎለብታል፡፡**





**ሌላው በአዋጅ ቁጥር 267/2011 ማሻሻያ የተደረገበት ስልጣንና ተግባር በነባሩ አዋጅ ቁጥር 186/2003 በአንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 2 ስለ ኦዲት ወሰንና የጊዜ ገደብ አስመልክቶ የተገለጸው ነው፡ ፡**

- መ/ቤቱ የኦዲት ሥራ ሲያከናውን ኦዲት ከሚደረግበት የበጀት ዓመት ወደኋላ ከአንድ በጀት ዓመት ማለፍ የለለበት ሆኖ ወንጀል ተፈጽሟል ተብሎ ከታመነ አምስት አመት ወደኋላ አልፎ ኦዲት ሊያደርግ ይችላል በሚል የተገለጸው ነጥብ በአዲሱ አዋጅ ኦዲት ከሚያደርግበት በጀት ዓመት ወደኋላ ከአምስት ዓመታት መብለጥ የለለበት ሆኖ ወንጀል ተፈጽሟል ተብሎ ከታመነ ወደኋላ እስከ 10 ዓመት ያለን ጉዳይ ኦዲት ከማድረግ አይታገድም በሚል ተሻሽሏል፡ ፡
- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ [2] ስር የተደነገገው ቢኖርም ለኦዲት ውጤቱ አስተማማኝነትና ሕጋዊነት አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን የሚያቀርቡና መረጃዎችን የሚሰጡ ብሎም ተጠያቂ የሚሆኑ አካላት በተለያዩ ተጨባጭ ምክንያቶች አለመኖራቸው በዋና ኦዲተሩ ከታመነበት ሥራው እንዳይጀመር ወይም የተጀመረው እንዲቋረጥ ዋና ኦዲተሩ ሊወስን እንደሚችል ተደንግጓል፡ ፡

**በአዋጅ ቁጥር 186/2003 በአንቀጽ 21 ስለ ኦዲት ተደራጊዎች ግዴታ የሚገልጸው 4 ንዑስ አንቀፆች የነበሩት ሲሆን በዚህ ማሻሸያ አዋጅ 5ኛ ንዑስ አንቀጽ እንደሚከተለው ተጨምሯል፡ ፡**

- መ/ቤቱ ከአንድ በላይ ማለትም ሁለት ምክትል ዋና ኦዲተሮች እንዲኖሩትና አንደኛው የቴክኒክ ዘርፉን ሁለተኛው የአስተዳደር ዘርፉን በመምራት ዋና ኦዲተሩን እንዲያግዙ እንዲሁም ዋና ኦዲተሩ በማይኖርበት ጊዜ ለየዘርፋቸው የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች የውክልና ደብዳቤ ሳያስፈልጋቸው እርሱን ተክተው መሥራት የሚችሉ ስለመሆኑ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

**ሌላው በአዋጅ ቁጥር 186/2003 ያልነበረና በአዋጅ ቁጥር 267/2011 ከመ/ቤቱ መዋቅር አንፃር የተካተተው ነጥብ የቅርንጫፍ ጽቤት ኃላፊ /አስተባባሪ/ስልጣንና ተግባር እንዲካተት የተደረገ ሲሆን የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሃላፊው[አስተባባሪ] የተሰጡት ስልጣንና ተግባራትም** ፡-

- በሥራቸው በታቀፉ የያካባቢው መንግስታዊ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሥራዎችን ከዋናው መ/ቤት የሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት ያቅዳሉ፣ ያደራጃሉ፣ ይመራሉ፣ ያስተባብራሉ ይከታተላሉ፡፡
- በሥራቸው የተመደቡ ዳይሬክቶሬቶችን፣ ኦዲተሮችንና ሌሎች የአስተዳደር ሠራተኞችን በቅርበት ሆኖ የመምራት፣ የማስተዳደርና ከዋናው መ/ቤት ጋር በመመካከርና በመቀናጀት የቅጥር፣ የዝውውር፣ የምደባ፣ ስምሪትና የድስፕሊን ጉዳዮችን የሚያከናውኑ ስለመሆኑ፡፡
- ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተመደበውን በጀትና ማንኛውም ሃብት ወይም ንብረት ከዋናው መ/ቤት የሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር በአግባቡ ሥራ ላይ የማዋልና ፤ ሥራ ላይ ስለመዋሉ የመከታተል ተግባር፡፡





## የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃ፣ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003

**ይህ የ3ኛ ዙር የአዋጅ ማሻሻያ እንዲደረግ ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች መካከል በወቅቱ የተካሄደው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት አሠራር ለውጥ ጥናት [BPR) ፣ የBPR ጥናቱን ተከትሎ የተገኙ ለውጦች ፣ የመ/ቤቱን ገለልተኝነት፣ ሙያዊ ነፃነትና አሠራርን ይበልጥ ለማሻሻል የሚሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ነበሩ፡፡**

- በዚህም መሠረት ከመ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር አንፃር መ/ቤቱ የኦዲት ሽፋኑን በመንግስት በጀቶች ላይ ይበልጥ ትኩረት አድርጎ እንዲያሳድግ በሚል እሳቤ በአዋጅ ቁጥር 98/1996 የመንግሥት ፕሮጀክቶችን በተቋራጭነት ለመሥራት ውል የገቡ የግል ባለሃብቶችን ሂሳብ ኦዲት እንዲያደርግ የተቀመጠው ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 186/2003 ከስልጣንና ተግባሩ ዝርዝር እንዲወጣ ወይም እንዲነሳ ተደርጓል፡፡
- የዋና ኦዲተር መ/ቤቱን ሙያዊ ነፃነት ይበልጥ ከማጠናከር አንፃር የወጡ ድንጋጌዎችን ስናይ ደግሞ ዋና ኦዲተር መ/ቤቱ እና ዋና ኦዲተሮች ተጠሪነታቸው ለክልሉ ምክር ቤት ብቻ እንዲሆን በዚህ የማሻሻያ አዋጅ በግልጽ መቀመጡ፣
- ዋና ኦዲተር መ/ቤቱ በጀቱን በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ እንዲያጸድቅ ስልጣን የተሰጠው መሆኑ፣

በክልሉ ለሚገኙ የሒሳብ ባለሙያዎች የሂሳብ አዋቂነትና የኦዲተርነት ሙያ በግል ለመሥራት የሙያ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የመስጠት፣ የመከታተል፣ የማደስ ብሎም የመሰረዝ ስልጣን መስጠቱ፤ በክልሉ የገንዘብና ንብረት ነክ አስተዳደር ጉዳዮች በሚወጡ መመሪያዎች ላይ ሙያዊ ምክር መስጠት የሚችል ስለመሆኑ የሚሉት በማሻሻያው የተካተቱ ነጥቦች ነበሩ፡፡

**ይህም አዋጅ ነባሩን አዋጅ ሙሉ ለሙሉ ተክቶ የተዘጋጀ ነው ፡፡**

## የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 267/2011

ይህን አዋጅ በመ/ቤቱ መቋቋሚያ አዋጅ ታሪክ ለሩኛ ጊዜ ማሻሻያ የተደረገበት ሲሆን አዋጁን ለማሻሻል እንደመነሻ የተወሰዱ ጉዳዮችም የመ/ቤቱ አደረጃጀት ለውጥ፤ የሠራተኞች አስተዳደር መቀየር፣ የኦዲት ሽፋንን ማሳደግ እና የኦዲት ሥራን በውክልና ማሠራት ስለሚቻልበት ሁኔታ የአሠራር መመሪያዎችን ማውጣት የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ይህ የማሻሻያ አዋጅ ሶስት ክፍሎችና 12 አንቀጾችን የያዘ ሲሆን ከነባሩ አዋጅ ቁጥር 186/2003 ጋር ጎን ለጎን በሥራ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት





- የመ/ቤቱ ሠራተኞች አስተዳደርን አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 186/2003 ላይ የመ/ቤቱ ሠራተኞች በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህግና ደንብ የሚተዳደሩ ሆኖ በተለዬ ሁኔታ የክልሉ መ/ቤቶች ቅጥር፤ ዝውውርና የደረጃ እድገት ላልተወሰነ ጊዜ በሚታገዱበት ወቅት እገዳው የዋና ኦዲተር መ/ቤትን የማይመለከተው ስለመሆኑ ተደንግጎ የነበረ ሲሆን በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 267/2011 ግን የሠራተኞች አስተዳደር በሁለት ተከፍሎ የአስተዳደር ሠራተኞች በነባሩ አዋጅ በተገለጸው አግባብ በሲቪል ሰርቪስ ህግና ደንብ መሠረት መተዳደራቸውን እንዲቀጥሉ ሆኖ ኦዲተሮችን በተመለከተ መ/ቤቱ የመዋቅርና የደመወዝ እስኬል በማዘጋጀትና በክልሉ ምክርቤት እንዲጸድቅ በማድረግ ደመወዛቸውንና ጥቅማጥቅሞቻቸውን —ክፍያ መፈጸም እንደሚቻልና ዝርዝር አፈፃፀሙን አስመልክቶ በምክርቤቱ በኩል የማስፈጸሚያ ደንብ እንደሚወጣ ተመላክቷል፡፡
- የኦዲተሮችን የሰው ሃይል ስምሪት አፈፃፀም በተመለከተ መ/ቤቱ በሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ሕግና ደንብ ውስጥ የተመለከቱ መሠረታዊ ዓላማዎችን ጠብቆ የሰው ሃይል ስምሪት ደንብና መመሪያዎችን በክልሉ ምክርቤት በማስጸደቅ ለመ/ቤቱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የኦዲተሮችን ቅጥር፣ ዝውውር፣ ደረጃ እድገት ፣የማስተዳደርና የስንብት ተግባራትን በሚጸድቀው ደንብ መሠረት መፈጸም እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡

**በነባሩ አዋጅ አንቀፅ 7 እና 8 የመ/ቤቱን አደረጃጀትና የሠራተኛ አሠተዳደር በተመለከተ የተገለጹት ነጥቦች በአዲሱ አዋጅ ከጄኢጅ( JEG) ጥናት ጋር ተያይዞ የስያሜና የአደረጃጀት ለውጦች የተደረገባቸው ሆኖ እናገኛለን፡፡**

በዚህም መሠረት በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 7 በንዑስ አንቀፅ 1 ከፊደል ተራ “ሐ” እስከ “ሠ” እና ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከቱት ዝርዝር ተግባራት በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 267/2011 ላይ ከዚህ በታች በተገለጹት ስልጣንና ተግባራት ተተክተዋል፡፡

ሐ. የኦዲት ዳይሬክተሮች፣ የሥራ ሂደት ባለቤቶችና አስተባባሪዎች ይል የነበረው የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ወይም አስተባባሪዎች በሚል ተተክቷል፤

መ. የኦዲት ማናጀሮች የሚለው የየዘርፉ ዳይሬክቶሬቶች በሚል ተተክቷል፤

ሠ. ሌሎች ኦዲተሮች የሚለው ሌሎች ኦዲተሮችና ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች በሚለው የተተካ መሆኑ፤

- በነባሩ አዋጅ በንዑስ አንቀፅ-2 የተመለከተው ከላይ በተጠቀሱት የስያሜ ለውጦች መነሻነት የመሠሪያ ቤቱ የሥራ አመራር በዋና ኦዲተሩ የሚመራ ሆኖ ምክትል ዋና ኦዲተሮችን ፣የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሃላፊዎችን ፣የየዘርፉን ዳይሬክቶሬቶች እንደአስፈላጊነቱ የኦዲት ቡድን መሪዎችን ወይም ኦዲት ማናጀሮችን ሊያካትት ይችላል በሚል ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡





**ከዚህ በመቀጠል ከነባሩ አወጅ ማሻሻያ የተደረገባቸውንና የተቀየሩ አንቀፆችን ለግንዛቤ እንዲሆን ለማሳየት እንሞክራለን፡፡**

- ከቃላት ትርጓሜ አንፃር በአዋጅ ቁጥር 186/2003 “ትርጓሜ” በሚለው አንቀፅ 2 ሥር የተመለከቱት 4 የቃላት ትርጓሜዎች ብቻ የነበሩ ሲሆን በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 267/2011 7 የቃላት ትርጓሜዎች በተጨማሪነት እንዲካተቱ ተደርገዋል እነሱም፡-

1. “**መሥሪያ ቤት**” የሚለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማለት ነው፡፡

2. “**ኦዲተር**” የሚለው በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ውስጥ በፋይናንስና ህጋዊነት ፣ በክዋኔ ፣ በኦዲት ምርመራና ስርጸት ፣ በልዩ ኦዲትና በሌሎች የኦዲት አይነቶች በየትኛውም ደረጃ በኦዲተርነት ተመድቦ በቋሚነትም ሆነ በኮንትራት ተቀጥሮ የሚያገለግል ሙያተኛ ማለት ነው፡፡

3. “**ዋና ኦዲተር**፣ እና “**ምክትል ዋና ኦዲተር** “ የሚለው በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግስት አንቀፅ 116 ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ መሠረት መ/ቤቱን ለመምራት የተሾሙ የሥራ ሃላፊዎች ማለት ነው፡፡

4. “**አለም-አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች**” የሚለው በዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች ድርጅትና የአፍሪካ ዋና ኦዲተሮች ተቋም አማካኝነት በየጊዜው እየተሻሻሉ በሥራ ላይ የዋሉትና ሃገራችን የተቀበለቻቸው ዓለም-አቀፋዊ የኦዲት አሠራርና አፈፃፀም ደረጃዎች ናቸው፡፡

7. **በዚህ የማሻሻያ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ** የተገለጸው ሁሉ የሴትንም ፆታ ይጨምራል የሚሉት ቃላቶች እንደ አዲስ ተካተውበታል፡፡

**ከመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር አንፃር በአዋጅ ቁጥር 186/2003 በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ከፊደል ተራ ኘ ፲ ነ እና ኘ የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት በአዲሱ አዋጅ እንደሚከተለው ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል፡፡**

- ከዚህ በፊት በነበሩት አዋጆች በግላቸው የሙያ ፈቃድ አውጥተው የሚሠሩ ኦዲተሮች ቀጥታ ከመንግስት በጀት የሚመደብላቸውን ተቋማት ኦዲት ማድረግ የማይችሉ የነበረ ሲሆን በዚህ አዋጅ መ/ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሥራን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ላላቸው የግል ኦዲተሮች ኦዲት እንዲያደርጉ በመስጠት የኦዲት ደረጃውን ጠብቆ ስለመከናወኑ የመቆጣጠርና የማረጋገጥ ሥራ መሥራት እንደሚችል ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
- በሌላ በኩል መ/ቤቱ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲትን በግል ኦዲተሮች ማሠራት እንዲችል አቅም ያላቸውን ለመምረጥ የሚያስችል የመመልመያ መስፈርቶችንና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚወስን ዝርዝር የአፈፃጸም መመሪያ ማውጣት እንደሚችል ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
- በግል ለሚሠሩ የተፈቀደላቸው ኦዲተሮችና ሂሳብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፣ የማደስ፣ የመሰረዝ ወዘተ በነባሩ አዋጅ ቁጥር 186/2003 ተካቶ የነበረ ቢሆንም ስልጣንና ተግባሩ





- ይህ ተግባር በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 267/2011 ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ውክልና ሲሰጠው በክልሉ ውስጥ ለሚኖሩና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ዝቅተኛ መስፈርቱን አሟልተው ለሚያመለክቱ ባለሙያዎች በኦዲት ሙያ ወይም በሂሳብ አያያዝ ሥራ ለመሰማራት የሚያስችላቸውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ይከታተላል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሠርዛል፣ ስልጠናና ምክር ይሠጣል፣ ሚሰጣቸው አገልግሎቶቾም ተገቢውን ዋጋ ማስከፈል እንደሚችል ተገልፇል፡፡

**በሌላ በኩል በአዋጅ ቁጥር 186/2003 ያልነበሩ ሁለት ተግባሮች እንደ አዲስ እንዲካተቱ የተደረገ ሲሆን እነሱም፡-**

- ከላይ ዋና ኦዲተር መ/ቤቱ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲትን በውክልና ማሠራት እንደሚችል በተገለጸው አግባብ ተግባሩ ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ የክልሉ መንግስት እንደ አስፈላጊነቱ በራሱ ገቢ የሚተዳደርና በሙያው ለክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተጠሪ የሆነ ክልላዊ የኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ሊያቋቁም እንደሚችልና ዝርዝር አደረጃጀቱም በደንብ እንደሚወሰን ተደንግጓል፡፡
- ሌላው በአዋጅ ቁጥር 186/2003 ያልነበረና በአዋጅ ቁጥር 267/2011 እንዲካተት የተደረገው ስልጣንና ተግባር የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶችና የህዝብና የመንግስት ጥቅም ያለባቸው አካላትን አስመልክቶ ኦዲት እንዲደረጉ በፍትሕ አካላትና በሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተቋማት የሚቀርቡ ትዕዛዝና ጥያቄዎችን በመቀበል ኦዲት ሊያደርግና